# “ በእውኔ ነው በህልሜ ? ”

## ‘ ለቅንጅት መረዎች ማስተዋሻ’

በህገሬ ሰማይ ከአጥናፍ እስከ አጥናፍ፤
ፍንትው ባለው ሕዋ በምናብ ስጠድፍ፤
ባሃሳብ መንኰራኩር ሌት ከቀን ስከንፍ፤
አየሯን ስቀዝፈው አድማስ ተሻግሬ፤
በየብሷ ሳንዃብብ በጭንቅ ተወጥሬ፤
እንቅልፌን አጥቶ ‘በምሰማው’ ወሬ፤
ሲቆስሉ ቆስዬ ሲታሰሩ አብሬ፤
በወገኔ መርዶ ሃዘን አቀርቅሬ፤
በሃገሬ ስቃይ ባህር ተሻግሬ፤
ልቤ ሲኰበልል በድኔን ተገትሬ፤
የምተነብየው መላ ተቸግሬ፤
አንጋጥጬ ሰማይ ከዋክብት ቆጥሬ፤
ህልሜ ቅዠት ይሆን ሳልፈታው ማደሬ፤
በእውኔ ነው በሕልሜ አይኖሩ መኖሬ።

ዳግም ነግቶ መሽቶ ከንቱው ቅብብል፤
የጐሸው ሳይጠራ ማዕበሉ ሳይጎድል፤
በዳር ስንከራተት መንፈሴ ሲጠል፤
በሀገሬ ስቃይ በወገኔ ቁስል፤
በስጋት በቁጭት በመንጠቋለል፤
በሃሳብ ደመና በመንቀዋለል፤
ለሰው-ለፈጣሪ ደጅ ጥናት ስውል፤
ሁለት በጋ-ክረምት ጸሎት ስማለል፡
ከአንድ እግሬ አንድ ጐኔ ሳልደላደል፤
እንደ ‘አባ ተክልዬ’ ሱባየን ስከፍል፤
በዘመን መባቻው ሰማሁኝ እልልል።
በእሥራተ-ዓመቱ ምህረት ሲታደል፡
እግር-ብረት ወልቆ ሰው ሲሸማገል፤
‘እድሜ ይፍታው’ ታስሮ ነፃ ግልግል፤

# በእውኔ ነው በህልሜ ?

‘ይሙት በቃው’ ሙቶ ፍርዱ ግምድልድል፤
የቃሊቲው ችሎት የዘመኑ ገድል፤
ከህልሜ አባነነኝ እውን እንዳስተውል።

ተፈቱ አሉ እስረኞች ጀግኖች በከፊል፤
ብርሃኑም ነጋ፤ ኃያሉ ሻውል፤
እህታችን ንግሥት፤ ሙሉነህ እዮል፤
ፍሬዋ ያማረች ብርቱካኗ ሰብል፤
የተናፈቁቱ መስፍንም ያቆብ፤
ሌሎችም ብርቅዮሽ ስማቸው ያብብ፤
ደምቀው የሚያበሩት እንደ አጥቢያ ኰከብ፤
እስዬም አብርሃ ደስታው ድርብርብ፤
ብረሪ ክነፊ የሰላም አርግብ፤
ይሁን ሁለት ሺህ  የሰላም መርከብ።

እርቅ ፍቅር ይውረድ ከዳር እስከ ዳር፤
ለትውልድ የሚበጅ ለሕዝብ ለሀገር፤

‘በቅድስት-ዮኃንስ የፍትህ መንበር’፤
ድንገት ወርዶ ይሆን እግዚአብሄር በምድር፤
ሊያምኑት የሚያዳግት የቅጽበት ታምር፤
ይኸ የመልካም ዜና ታልቁ ጅምር፤
የተሰፋው ጭላንጭል  እንዲከፍት በር፤
አሳሪ ይታሰር የሕዝብ የሃገር።

# በእውኔ ነው በህልሜ ?

በእስር ቤት ታጅለው ሰንናፍቃቸው፤
ከርመን ስንሰላቸው ስናበጃጃቸው፤
የኛ ‘ማንዴላዎች’ የአሞካሸናቸው፤
የቅንጅት ጅግኖች በአቋም ጽናታቸው፤
በአንድነት የሚያምኑ በቃል ኪዳናቸው፥
የዘመኑ አርበኞች አቻ የሌላቸው፤
ከመካከላችን በመገኘታቸው፤
እጡብ ድንቅ ነበር አቀባበልቸው።

ከሞት አፋፍ ተርፈው ከሲያል ዘብጥያ፤
ጀግኖቻችን መጥተው ሳለ ‘ፈንጠዚያ’
በአውሮፓ አሜሪካ በዓላማችን ዙሪያ፤
ናፍቆት ተለዋውጠን በዘመድ ገበያ፤
ማቅናት እንጅ ፍቅር የሰላም ቡቃያ፤
ጸብ ትርፉ ኪሳራ ሽሙጥ በዓለም ማያ።

ቋጥረን ያቆየነው የቃል ኪዳን ሚስጥር፤
ሺህ የአስተሳሰረው እንደ እትብት በፍቅር፤
የአጠለቅነው እምነት የአንድነት ማተብ-ክር፤
የክብራችን ካባ ግማዱ ባለ ሐር፤
ባህር ማዶ ጡዞ ተፍተልትሎ ቢከር፤
የአጠነጠኑበት አንደበት ቢያሻክር፤
ውሉ እንዳይቆረጥ አንገት እንዳይሰብር፤
‘ነጠላው ቅንጅት’ ማጣፊያው እንዳያጥር፤
ንፋስ እንዳይገባው እርቃኑን እንዳይቀር፤

# በእውኔ ነው በህልሜ ?

**ለጠላቶቻችን ፍንካካ ሳይፈጥር፤**
**የመሪዎቻችን ዳግም ቁም-አሳር፤**
**አለ ወይ እስር ቤት በነፃው ምድር፤**
**ተንቀሳቃሽ ወህኒ የሚያነቋቁር፤**
**ምን በደል አለና የማያናግር/የማያማክር፤**
**ወይንስ በአስር ናችሁ 'ሰፋ ባለው አጥር'፤**
**እስኪ መላ በሉኝ ተኘቸ ልደር፤**
**በእውኔ ነው በህልሜ የምደናገር።**

**የጐንቸው፡**
yegonchaw@yahoo.co.uk

*የቅንጅት መሪዎቻችን ከእስር ቤት ወጥተው በሀቅ የቆሙለትን የኢትዮጵያን ሕዝብ ሙሉ ነፃነቱንና ዲሞክራሲያዊ መብቱን ለማጐናጸፍ የጀመሩትን 'ባለ ብዙ ራዕይ' ትግል እንዲቀጥሉ ባደረግነው ያላሰለሰ ትግል እነሆ ከቃሊቲ እስር ቤት ወጥተው ከመካከላችንም ለመገኘት በቅተዋል፡ ይህ ታሪካዊ ሰሞን እጅግ የተደሰትንበትና ምንጊዜም የምናስታውሰው ይሆናል።*

*በሌላ በኩል በቅርቡ በመሪዎች መካክል 'ተከሰቷል' በሚባለው 'የልዩነት ጥርጣሬ' ከሁሉም በላይ ድንጋጤን፤ሥጋትንና ሃዘንንም እየፈጠረ ይገኛል፣ ይሁንና 'የፓርቲውን ህልውና የሚፈታተን ችግር' ካለ በውይይት ለመፍታት አቅሙም ፍላጐቱም የሚያንሳቸው መሪዎች አይደሉም፡ በተጨማሪም ይህንን ለማፋጠንና ለማሳካት በቅርብ ሁነው አቅሙና አጋጣሚው የሚፈቅድላቸውን ሁሉ የተቻላቸውን ጥረት እንዲያደርጉ እየተማጸን ሌሎች ደጋፊዎች ጠላትና ምቀኞች በመቀባበል የሚያባዙትን 'ጥራዝ ነጠቅ' ወሬና ሽኩቻ ለጊዜው በትግሥትና በትልቅነት እንዲታዘቡት ይሆን።*

*እንደ እኔ ግምት ከሆነ እነዚህ ታልቅ 'ባለ ብዙ ራዕይ' መሪዎች እንኳንስ አንድ ዓላማ ባላቸው የትግል አጋሮቻቸውና ጓደኞቻቸው መካከል ይቅርና ሞት እና እድሜ ልክ ከሚፈርጅባቸው፤የቁም ሰቅል ካሳያቸው ጠላት፤ ወያኔ ጋር እንኳን በብስለትና በትዕግሥት ተወያይተው በአሸናፊነት የሚዘልቁ ጀግኖች ይመስሉኛል፤ ስለሆነም ጉዳዩ በቅርቡ በግልጽ እስኪታወቅ ድረስ ይህንን ክስተት እንደ ውይይት ሂደት እንጅ እንደ 'የዓለም ፍፃሜ' አጋነን አንየው እላለሁ።*